ከሙስና የጸዱች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

ፀረ-ሙስና ቅጽ 2 ቁጥር 23 ሀምሌ 30/2017 ዓ.ም

## በውስጥ ገጾች

ኮሚሽነር ሳሙኤል ኡርቃቶ (ፒ.ኤች.ዲ.) ከአሜሪካ አምባሳደር ከተከበሩ ኢቬሪን ማሴንጋ ጋር ተወያዩ
ገጽ 2

በበጀት ዓመቱ ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል አበረታች ሥራዎች ተሰርተዋል
ገጽ 4

የጋምቤላ ክልል ምክር ቤት 3 የከፍተኛና 2 የመጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኞችን ከሥራ እንዲሰናበቱ ወሰነ
ገጽ 4

## 14ኛው አገርአቀፍ የሥነምግባርና የፀረ- ሙስና ኮሚሽኖች ትስስር ጉባኤ የተለያዩ ውሳኔዎችን አሳለፈ

### ትስስር ጉባዔው የ2017 በጀት አመት አገራዊ የፀረሙስና ትግል እንቅስቃሴ እና የ2018 በጀት አመት እቅድ ላይ መክሯል



14ኛው አገርአቀፍ የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች ትስስር ጉባኤ የተለያዩ ውሳኔዎችን አሳለፈ። የጉባኤው ሙሉ መግለጫ እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

ሙስና የአንድን አገር መልካም አስተዳደር፣ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ እና የሰላም አለመረጋጋት ከሚፈጥሩ ችግሮች መካከል አንዱ እና ዋነኛው ነው፡፡ የፀረ ሙስና ትግል ውስብስብና አስቸጋሪ እየሆነ የመጣ ዓለም አቀፍና አገር አቀፍ ችግር በመሆኑ ትግሉን ይበልጥ ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግ ጊዜው የሚጠይቀውን የአሰራር፣ የትብብርና የቅንጅት ስራን ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊና ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ፈርማ እና አፅድቃ የሕጓ አካል ያደረገቻቸውን የተባበሩት መንግስታት የፀረ ሙስና ኮንቬንሽን እና የአፍሪካ የፀረ ሙስና መዋጊያና መከላከያ ኮንቬንሽን እንደሀገር የፀረ ሙስና ትግሉን የማስተባበር ኃላፊነት የተሰጠው የፌዴራል ሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን በፀረሙስና ትግሉ ሚና ያላቸውን አካላት በመምራት እና በማስተባበር በርካታ ስራዎች ሲከናወኑ ቆይተዋል፡፡

ወደ ገፅ 6 ዞሯል

## የኮሚሽኑ አመራር እና ሰራተኞች በ2018 ሀገራዊ የልማት ዕቅድ ላይ ውይይት አካሄዱ





የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን አመራር እና ሰራተኞች በ2018 ሀገራዊ የልማት ዕቅድና የፀረሙስና ትግል የውይይት መድረክ አካሂደዋል። በዉይይት መድረኩ ላይ የኮሚሽኑ አመራሮችና ሰራተኞች በቀረበው ሀገራዊ እቅድ መነሻ በማድረግ ውይይት የተደረገ ሲሆን ከመድረኩም የተለያዩ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ሰተጥተዉ መልስ ተሰጥቷል፡፡ የ2018 በጀት ዓመት ሀገራዊ የፀረ-ሙስና ዕቅድ እንዲሳካ ሁሉም ሃላፊነቱን እንዲወጣ የኮሚሽኑ ኮሚሽነር ሳሙኤል ኡርቃቶ (ዶ/ር) አሳስበዋል፡ ፡

# የፌደራል የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን አመራርና ሠራተኞች የአንድ ጀንበር አረንጓዴ አሻራ መርሀ-ግብር አካሄዱ

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረሙስና ኮሚሽን አመራር እና ሰራተኞች በአንድ ጀምበር 7 መቶ ሚሊዮን ችግኝ የመትከል መርሐግብር አካሂደዋል፡፡

ሀምሌ 24/2017 ዓ.ም በአገር አቀፍ ደረጃ በመትከል ማንሰራራት በሚል መሪ ቃል በአንድ ጀምበር ሰባት መቶ ሚሊዬን የመትከል ዘመቻ የኮሚሽኑ አመራርና ሰራተኞች ችግኝ የመትከል መርሃ ግብር በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 አካባቢ ተከናዉኗል፡፡





# ኮሚሽነር ሳሙኤል ኡርቃቶ (ፒ.ኤች.ዲ.) ከአሜሪካ አምባሳደር ከተከበሩ ኢቬሪን ማሴንጋ ጋር ተወያዩ




የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ሳሙኤል ኡርቃቶ (ፒ.ኤች.ዲ.) ከአሜሪካ አምባሳደር ከተከበሩ ኤቪሪን ማሲንጋ ጋር ተወያይተዋል፡፡ ውይይቱ በፀረ-ሙስና ትግል እና ተያያዥ ወንጀሎች ዙሪያ በትብብር በሚሰሩ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ነው፡፡





# ዕጩ የሥነምግባር አምባሳደሮች በክረምት በጎ ፈቃድ ስራ ላይ ተሰማሩ

የፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በ2017 በጀት ዓመት ካከናወናቸው ዋና ዋና ተግባራት ውስጥ በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎችን በእጩ የሥነምግባር አምባሳደርነት አወዳድሮ እውቅና መስጠቱ ይታወቃል፡፡ በዚህ መሠረት 220 እጩ የሥነምግባር አምባሳደሮች በክረምት በጎ ፈቃድ ስራ የሚሳተፉባቸውን አካባቢዎች መረጃ በመለየት ሥምሪት የመስጠት ሥራ የተከናወነ ሲሆን በዚህም መሠረት የሥነ-ምግባር ትምህርት በማስተማር፣ የአቅመ ደካሞችን ቤት ማደስና በመስራት፣በከተማና በገጠር ኮሪደር ልማት፣ ችግኝ ተከላ፣ፖሊሳዊ አገልግሎት/ትራፊክ አገልግሎት፣ ወንጀልን በመከላከል፣ የክረምት ትምህርት ማስተማር እና እንደየ አካባቢያቸው የሚሰሩ የበጎ ፈቃድ ስራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡

## የሥነምግባር እጩ አምባሳደር የሆነው ተማሪ በማዕረግ ተመርቆ ዩኒቨርስቲው የስራ እድል አመቻችቶለታል፡፡




# በበጀት ዓመቱ ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል አበረታች ሥራዎች ተሰርተዋል:-

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

በተጠናቀቀው የ2017 በጀት ዓመት ከሙስናና ብልሹ አሰራር ጋር በተያያዘ ከቀረቡ ጥቆማዎች ውስጥ ለ17ቱ የውሳኔ ኃሳብ ለሚመለከተው ክፍል መቅረቡን የኢትዮጵየ ኤሌክትሪክ ሃይል የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና መከታተያ መምሪያ ገለፀ፡፡

በመምሪያው የሙስና ተጋላጭነት ጥናት እና ሥልጠና ሥራ አስኪያጅ አቶ መንግስቱ አባይነህ እንደገለፁት በበጀት ዓመቱ ከግዢ ሂደት፣ ከፕሮጀክት አመራር፣ ከጥቅም ግጭት፣ ከካሳ ክፍያ አፈፃፀም እና ከአስተዳደር ጋር የተያያዙ 18 ጥቆማዎች ቀርበዋል፡፡ ከቀረቡት ጥቆማዎች መካከል በ17ቱ ላይ አስፈላጊውን የማጣራት ሥራ በማከናወን ለሚመለከተው አካል የውሳኔ ሀሳብ መቅረቡን ተናግረዋል፡፡

ሥራ አስኪያጁ አክለውም ለቢሮው የቀረቡ 3 የአስቸኳይ የሙስና መከላከል ጥቆማዎች ተጣርተው የማስተካከያ እርምጃዎች መወሰዳቸውንም አብራርተዋል፡፡ ቢሮው ሠራተኞችና የሥራ መሪዎች በሥነምግባር የታነጹ እንዲሆኑ፣ ሙስናን እንዲጸየፉ እና እንዲከላከሉ የሚያስችል የስልጠና ሞጁል በማዘጋጀት በሙስና ተጋላጭነት እና በሥነምግባር ጽንሰ ሀሳብና ሙስና መከላከል ስትራቴጂ ዙሪያ ለ60 የሥራ ኃላፊዎች እና ለ120 ሠራተኞች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠቱን አስታውሰዋል፡፡

በበጀት ዓመቱ 1 ሺ 572 የሥራ መሪዎችና ሠራተኞች ሀብታቸውን ማስመዝገባቸውን የጠቆሙት አቶ መንግስቱ ከፌዴራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን፣ ከገንዘብ ሚኒስቴር እና ኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ ጋር በመተባበር የፀረ-ሙስና ንቅናቄ ሥራዎችን ቢሮው እያከናወነ መሆኑን አብራርተዋል፡፡ በተጨማሪም የጥቅም ግጭትን ለመከላከል የሚያግዝ ጥናት ለማካሄድ መረጃዎች ተሰብስበው ለኮሚሽኑ መላካቸውን አስገንዝበዋል፡፡

የኢትዮጵየ ኤሌክትሪክ ሃይል የሥነምግባርና ፀረ-ሙስና መከታተያ መምሪያ ዳይሬክተር አቶ ደረጀ አጥናፌ በበኩላቸው የጥቅም ግጭት፣ ከሠራተኞች ሥነ-ምግባር እና ሙስናን ከመታገል አኳያ የአመራር ቁርጠኝነትን፣ ከጠቋሚዎች ከለላ እና ከጉቦ መከላከል ጋር በተያያዘ የተዘጋጁ ፖሊሲዎች በቅርቡ ወደ ሥራ ይገባሉ ተብሎ እንደሚጠበቅ ተናግረዋል፡፡

የሙስና ጥቆማ መቀበያውን ለማዘመንና ተደራሽ ለማድረግ ሶፍትዌር የበለፀገ ሲሆን ወደ ሥራ በሚገባበት ዙሪያ በቀጣይ ከኤ.ሲ.ቲ. እና ከሳይበር ደህንነት የሥራ ክፍሎች ጋር በትብብር እንደሚሰራ ገልፀዋል፡፡

በስራ ክፍሉ ያለው የሰው ኃይል በቂ ባለመሆኑ ሁሉም ሪጅኖች ላይ ተደራሽ መሆን አለመቻል፣ የግንዛቤና የመረጃ እጥረት መኖር በበጀት ዓመቱ የታዩ ክፍተት መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡ አቶ ደረጀ በቀጣይ በጀት ዓመት ለሁሉም የሥራ ኃላፊዎች ሥልጠና በመስጠት፣ ሕግና አሰራሮችን በመፈተሽ፣ ጠንካራ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋት እና ቅንጅታዊ አሰራርን በማሳደግ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ትኩረት ተሰጥቶ ይሰራል ብለዋል፡፡

## የጋምቤላ ክልል ምክር ቤት 3 የከፍተኛና 2 የመጀመርያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኞችን ከሥራ እንዲሰናበቱ ወሰነ

የጋምቤላ ክልል ምክር ቤት 2 የከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንቶች እና አንድ ዳኛ በፈፀሙት የሥነ ምግባር ጉድለት፤ ከሥራ እንዲሰናበቱ ወስኗል።

በተመሳሳይ ምክርቤቱ ሁለት የወረዳ ፍርድ ቤት ዳኞችንም ከሥራ አሰናብቷል። ምክር ቤቱ ለሁለት ቀናት ሲያካሂድ የነበረውን መደበኛ ጉባዔ የተለያዩ ውሳኔዎችን በማስተላለፍ በዛሬው ዕለት ማጠናቀቁን የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ዘግቧል።

የክልሉ ምክር ቤቱ የሙስና ወንጀል የፈፀሙ እና የሥነ-ምግባር ጉድለት ያሳዩ 4 የከፍተኛ እና የወረዳ ፍርድ ቤት ዳኞች ከደረጃ ዝቅ የማድረግ ውሳኔንም አሳልፏል።



## የዩክሬን ባለስልጣናት በወታደራዊ ድሮን ግዢ ወቅት በፈፀሙት የሙስና ወንጀል በቁጥጥር ስር ዋሉ

አንድ የዩክሬን የፓርላማ አባል እና ሌሎች ባለስልጣናት የአገሪቱ የፀረ ሙስና ኤጀንሲዎች በሰው አልባ አውሮፕላኖች እና የኤሌክትሮኒክስ የጦር መሳሪያዎችን ግዢ ሂደት የነበረን መጠነ ሰፊ ሙስና ካጋለጡ በኋላ በቁጥጥር ስር ዋሉ።

ፕሬዝዳንት ቮሎዲሚር ዜሌንስኪ በኤክስ ገጻቸው ላይ አንድ የዩክሬን ፓርላማ አባል፣ የአውራጃ እና የከተማ አስተዳደሮች እና በርካታ የብሔራዊ ዘብ አገልግሎት አባላት በዚህ ድርጊት ውስጥ ተሳትፈው ተገኝተዋል።

በዚህም የተነሳ መንግሥት ከአቅራቢዎች ጋር በገባው ውል ላይ እስከ 30 በመቶ የሚደርስ የዋጋ ጭማሪ በማድረግ እንደተፈራረሙ መፃፋቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።



## በወንጀል የተገኘ ሀብት ማስመለስና በፋይናንስ ወንጀል ምርመራ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ የውይይት መድረክ ተካሄደ

በፍትሕ ሚኒስቴር እና በተባበሩት መንግስታት የሕገወጥ መድሃኒት ዝውውር እና ወንጀል ቁጥጥር ቢሮ (United Nations Office on Drugs and Crime) በጋራ በተዘጋጀው የውይይት መድረክ የፍትህ ሚኒስቴር፣ የፌዴራል ከፍተኛና መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከፍተኛ አመራሮች፣ የስዊዘርላንድ አምባሳደር በኢትዮጵያ H.E Tamara Mona እና የUNODC የጸረ-ሙስና ማዕከል የቡድን መሪ Mr. Francesco Checchi ተገኝተዋል።

በመድረኩ ላይ የፍትህ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ተስፋዬ ዳባ በወንጀል የተገኘ ሀብት በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው የዓለም-ዓቀፍ ማህበረሰብ ሀብት ላይ በሚፈጸም ከፍተኛ ምዝበራ የሚገኝ ከባድ የሙስና የወንጀል ውጤት መሆኑን ጠቅሰው ለዚህም በተለያዩ ጊዜ በዓለም-ዓቀፍ ተቋማት በተሰሩ ጥናቶች በማደግ ላይ ካሉ ሀገራት ብቻ በየዓመቱ በአማካይ ከሁለት እስከ አምስት በመቶ የሚሆነው ጠቅላላ የሀገር ውስጥ ምርትን የሚሸፍን ሀብት የሚመዘበር መሆኑን በመጥቀስ በዚህ ከፍተኛ የሀብት እንቅስቃሴ ማንኛውም ማህበረሰብ ዋጋ እየከፈለ የሚገኝ እንደመሆኑ መጠን በሕግ የተለያየ ሃላፊነት የተሰጣቸው ተቋማት እና ሰራተኞቻቸው በተሻለ እውቀት እና መናበብ የሕግ የበላይነትን የማረጋገጥ ሃላፊነት እንደለባቸው ገልጸዋል ።

የፍትህ ሚኒስቴር ሚንስትር ወ/ሮ ሀና አርዓያሥላሴ በውይይት መድረኩ ላይ ተገኝተዉu ባስተላለፉት መልዕክት በወንጀል የተገኘ ሀብት በሀገር ኢኮኖሚ እና ማህበራዊ እድገት ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርስ መሆኑን በመጥቀስ ይህን የወንጀል ተግባር ለመከላከልና ለመቆጣጠር ዓለም-ዓቀፋዊ ትብብር እንደሚያስፈልግና ይህንን በተግባር ለማረጋገጥም ወቅቱን ያገናዘበ የሕግ ማዕቀፍ እንደሚያስፈልግ ገልፀው ይህንን የሕገ ማዕቀፍ ሀገራችን በቅርቡ ያጸደቀች መሆኑን አረጋግጠዋል፡ ፡ ኢትዮጵያ በወንጀል የተገኘ ሀብትን በማስመለስ ረገድ እያሳየች ያለውን ቁርጠኝት የሚያሳይ መሆኑን አንስተው በመድረኩ ተሳታፊ የሆኑ ዳኞች ፣ ዐቃቤያነ ሕግ፣ መርማሪዎች፣ የፋይናንስ አናሊስቶች፣ ጠበቆችና ሌሎች ተገቢነት ያላቸው ባለሙያዎች ከዚህ የውይይት መድረክ ሀገራችንን ማገዝ የሚችሉበትን የልምድ መጋራት እንደሚያደርጉ እና ዓለም-ዓቀፍ ሁኔታዎችን በመገንዘብ የጎላ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ተብሎ እንደሚጠበቅ ገልፀዋል። አያይዘውም የፍትህ ሚኒስቴር በአጠቃላይ በወንጀል የተገኘ ሀብትና የፋይናንስ ወንጀል ምርመራ ጉዳዮችን በተመለከተ ወደፊት በተቋማት ደረጃ፣ በሀገር-ዓቀፍ ደረጃ እንዲሁም ዓለም-ዓቀፍ መደረኮች እንዲዘጋጁ በማድረግ ኃላፊነቱን እንደሚወጣ አረጋግጠዋል።

መድረኩ በተባበሩት መንግስታት የጸረ-ሙስና ስምምነት የሀብት ማስመለስ ጉዳዮች ላይ በባለሙያ ማብራሪያ የተሰጠ ሲሆን ኢትዮጵያ በቅርብ ያወጣችው የንብረት ማስመለስ አዋጅ ይዘትና ዓላማ በባለሙያ ማብራሪያ ተሰጥቶበታል።







ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በየ15 ቀን የሚዘጋጅ ጋዜጣ

ፖ.ሳ.ቁ 34799
ኢ-ሜይል FeaccEthiopia2013@et
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ፌስቡክ www.facebook.com/feaccOfficial
ቴሌግራም t.me/feacc
ትዊተር www.twitter.com/EthiopiaFeacc
ዩቲዩብ Federal Ethics & Anti-Corruption Commission

**ለሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ስራዎች**
**EARS**

**ለፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና ወንጀል ጥቆማ መስጫ አድራሻዎች**

ሞባይል 0935947533

ፖ.ሳ.ቁ 34799
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ቴሌግራም t.me/CorruptionPointing
ዋትስኣፕ wa.me/qr/5IGXTSIYUMPBF1

**NCRS**

# ርዕሰ -አንቀፅ

## በህዝባዊ ተቋማት የብድር አሰጣጥ፣ ክትትልና አከፋፈል የሚፈጸምን የሙስና ወንጀል ግልጽና ፍትሀዊ አሰራርን በመዘርጋት ተቋማቱ ወንጀሉን መከላከል አለባቸው

የሙስና ወንጀል በማንኛውም መንግሥታዊ፣ መንግሥታዊ ያልሆኑና በተለያዩ ሕዝባዊ ድርጅቶች የሚፈጸም ቢሆንም ከገንዘብ ዝውውር ጋር ከፍተኛ ትሥሥር ባላቸው ህዝባዊ ድርጅቶች (በባንኮች፣ በመድህን ድርጅቶችና መሰል የፋይናንስ ተቋማት) ግን መቆጣጠር በሚያዳግት አኳኋን እየተስፋፋ ይገኛል፤ በተለይም "በውስጥ ሰራተኞች" አማካኝነት የሚፈጻም ሲሆን እጅግ በጣም ዉስብስብ ይሆናል ።

ህዝባዊ ድርጅቶች ለሙስና ያላቸዉን ተጋላጭነት የብድር አሰጣጥ፣ የህግ ተገዢነት፣ የደንበኛ/ተገልጋይ መስተጋብር፣ የሰነድ/መረጃ አየያዝና አጠቃቀም፣ እና የመሳስሉትን ያካትታል፣በብድር አሰጣጥ፣ ክትትልና አከፋፈል ላይ የብድር አሰጣጥ ሂደት መጓተት፣ የገንዘብ እጥረትና ተደራሽ ዓለመሆን የራሳቸው አስተዋፅኦ የሚያደርጉ ቢሆንም፣ በዚህ ረገድ ለሚፈጠር ችግር ሙስና ከፍተኛዉን ድርሻ ይወስዳል። በመሆኑም ከብድር ማረጋገጫ ሂደቶች፣ ከብድር ክትትልና አከፋፈል ጋር በተያያዘ ህዝባዊ ድርጅቶች ለሚከተሉት ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ሊጋለጡ ይችላሉ።

የባንክና የማይክሮ ፋይናንስ ሰራተኞች በብድር አሰጣጥ ረገድ የተበዳሪዎችን ቅደም ተከተል በማዛነፍ፣ በተጭበረበረ ወይም ባልተሟላ መረጃ ተመስርተው ወይም ተበዳሪው መያዣ ሳያቀርብ ብድርን በመፍቀድ እና ኮሚሽን ለመቀበል በመመሳጠር ኢ-ስነምግባራዊ ድርጊቶች ላይ ተሳትፎ ሊኖራቸው ይችላል። ብድር አመላለስን በተመለከተ በፋይናንስ ሴክተሩ ያሉ ሰራተኞች ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ፣ ብድሮች በሰዓቱና በአግባቡ እንዳይመለሱ፣ በመያዣነት የተያዙ ንብረቶችም ለብድሩ መሸፈኛ እንዳይዉሉ ወይም በርካሽ ዋጋ እንዲተላለፉ በመመሳጠር ስነምግባር በጎደለው ተግባር ዉስጥ ሊሳተፉ ይችላሉ።

ከላይ የተጠቀሱ ሁኔታዎች እንዲከሰቱ የብድር ፖሊሲ ጠቅለል ባለ መልኩ መቀመጥ አንዱ መንስኤ ሲሆን፣ መተንተን እና መተርጎም የሚገባቸውን ነገሮች በዝርዝር የሚያስቀምጥ ማኑዋል አለመኖር/አለመዘጋጀት ደግሞ ሌለኛዉ ምክንያት ነው። ለምሳሌ ያህል በልዩነት የሚታዩ ጉዳዮች በዝርዝር ምን ምን መሆን እንደሚገባቸው ግልፅ በሆነ መልኩ ካልተገለጸ የግልፅነት እና የተጠያቂነት ክፍተት ያስከትላል፤ በግለሰብ ውሳኔ ላይ የተመሰረተ አሰራር ወይም ውሳኔ እንዲኖር በማድረግም ለሙስናና ብልሹ አሰራር በር ሊከፍት እንደሚችሉ የፌዴራል የስነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የአሰራር ስርዓት ጥናት ሪፖርት ያመላክታል፡፡ እንዲህ ዓይነት ውሳኔዎች ደግሞ ከፍትሃዊነት ይልቅ በግላዊ ግንኙነቶች ተጽእኖ ስር ሊወድቁ ስለሚችሉ ፍትሃዊ ያልሆነ የብድር ስርጭትን ያስከትላሉ። በሌላ መልኩ እንዲህ ዓይነት ውሳኔዎችና ድርጊቶች ተበዳሪዎችን ግልጽ ላልሆኑ እና ላልተገቡ ክፍያዎች ከመዳረግም በላይ፣ ከዕዳ አዙሪት ውስጥ እንዳይወጡ ሊያደርጓቸዉ ይችላሉ። በዚህ መልኩ ተጋላጭ የሆኑ አካላት ሊበዘበዙ ይችላሉ።

የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ሙስናንና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል በስልጠና፣ በአሰራር ስርዓት ጥናትና በሌሎች መንገዶች እየሰራ ቢሆንም፣ ይህ ጥረት የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ትብብር ይፈልጋል። ስለሆነም ህዝባዊ ተቋማት የብድር አሰጣጥ፣ ክትትልና አመላልስ ግልጽና ፍትሃዊ የሆነ አሰራር በመዘርጋት ሙስናን ለመከላከል ወሳኝ ሚና መጫወት አለባቸው።

## ከ6 የዞረ.....

በተለይም የክልልና የከተማ አስተዳደር የሥነምግባርና የፀረሙስና ኮሚሽኖች ቀደም ሲል 13 ዙር ሀገር አቀፍ የትስስር ጉባኤዎችን ሲያካሄዱ ቆይተዋል፡፡

ከሐምሌ 25-26 2017 ዓ.ም ባካሄዱት 14ኛው ጉባኤ የትስስር መድረክ በ2017 በጀት ዓመት በመንግስት መ/ቤቶች፣ የልማት ድርጅቶች እና በህዝባዊ ድርጅቶች ሲከናወኑ በነበሩ የሥነምግባር ግንባታ እና ሙስና መከላከል ተግባራት የዕቅድ አፈፃፀም እና በ2018 በጀት ዓመት የአንድ ዕቅድ የአንድ ሪፖርት ላይ ውይይት ተደርጓል፡፡ ጉባኤው በዋናነት በ2017 በጀት ዓመት ሲከናወኑ በነበሩ የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ስራዎች በጥልቀት የተወያየ ሲሆን በጉባኤው ከተነሱ ዋና ዋና ጉዳዮች መካከል፡-

በሥነምግባር ግንባታ ፕሮግራም የሥነምግባር ስልጠና መስከ 26 ዘርፍ ተኮር የስልጠና ሞጁሎችን ከምሁራን ጋር በመተባባርና በማዘጋጀት እርሱን መሰረት ያደረገ 445,374 ሺህ ለሚሆኑ የተቋማት ከፍተኛ አመራሮችና ሠራተኞች ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡





በፀረ ሙስና ትግል ዙሪያ ሕዝብ ግንዛቤን ለማስረፅ በተሰራው ስራ 531 መድረኮች የሕዝብ ግንዛቤ ስራዎች፣ 57,386 በጋዜጣ እና በሌሎች ዘዴዎች እንዲሁም 2,079 የተሰሩ ሲሆን ሕብረተሰቡን በፀረ ሙስና ትግሉ ዙሪያ ግንዛቤ እንዲኖረውና ሙስናን እንዲታገል ተደርጓል፡፡

የሥነምግባር እና ፀረ ሙስና አስፈፃሚዎች አደረጃጀቶች በመጠቀም በየደረጃው ስራዎች የተሰሩበት ዓመት ከመሆኑም ባለፈ እንደ ሀገር ከ10,000 ሺህ በላይ የሚሆኑ የሥነምግባር ሰራዊት ተግባርና ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ በማድረግ በኩል ስራዎችን መስራት የተቻለበት ዓመት ቢሆንም ይበልጥ መጠናከር እንዳለበት ተመላክቷል፡፡

ሙስናን ቀድሞ በመከላከል አንዱና አዋጪው የፀረ ሙስና ትግል ስልት እንደመሆኑ መጠን በበጀት ዓመቱ እንደሀገር 127 የሙስና መከላከል ጥናት፣ 1,585 የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ስራ፣ ከ2.2 ቢሊዮን ብር በላይ የሆነ በገንዘብ እና 270,078 የከተማና የገጠር መሬት ከብክነት ማዳን ተችላል፡፡ የሙስና መረጃ የማመንጨት ስራ ጋር በተያያዘ በበጀት ዓመቱ 6,881 ጥቆማዎች ቀርበው የትንተና ስራ እና የተለያዩ ውሳኔዎች እንዲሰጥባቸው የተደረገበት ዓመት ነበር፡፡

በበጀት ዓመቱ ቀጠናዊ፣ አህጉራዊ፣ አለምአቀፋዊ በሥነምግባር ግንባታና በሙስና መከላከል ዙሪያ የፀረ ሙስና ትግሉን ለማጠናከር እና የፀረ ሙስና ስምምነቶችን ተግባራዊ ለማድረግ በተለያዩ መድረኮች ኢትዮጵያን የፀረ ሙስና ትግል የሚያንፀባርቁ ስራዎች የተሰሩበት ዓመት እንደነበር ጉባኤው ገምግሟል፡፡

መንግሥታዊ ሙስና አሁን ላይ ሥጋት ባይሆንም አስተዳደራዊ የአገልግሎት አሰጣጥ ጋር የተያያዙ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮች የላቀ ትግል የሚሹ መሆኑን ትስስር ጉባኤው ገምግሟል።

ተቋማዊ አቅም ከመገንባት አኳያ የአደረጃጀት፣ የአሰራር እና የሕግ የማሻሻያ ስራዎች የተከናወኑ ሲሆን ከዚህ በበለጠ ሁኔታ በፌደራልም ሆነ በክልል ያሉ የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች አደረጃጀት እና አሰራር የፀረሙስና ትግል አቅጣጫን ታሳቢ ያደረጉ ተግባራት ማከናወን እንደሚገባ ተመላክቷል፡፡

ጉባኤው ከላይ የተመለከቱትን የ2017 በጀት ዓመት አፈፃፀሞች ከገመገመ በኋላ ለ2018 በጀት ዓመት በሥነምግባር ግንባታና በሙስና መከላከል ስራዎች ታቅዶ የቀረበውን ሀገራዊ የአንድ እቅድ አንድ ሪፖርት ይበልጥ ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመተግባር እንዲያስችል ጉባኤው ውይይት አድርጎበታል፡፡

በመሆኑም እኛ የፌዴራል፣ የክልልና የከተማ አስተዳደር የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽኖች ከሐምሌ 25-27 ባደረግነው በ14ኛው ሀገር አቀፍ የትስስር ጉባኤ በ2018 በጀት ዓመት ከፍትህ አካላትና ለትግሉ አጋዥ ከሆኑ ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የፀረ-ሙስና ትግል ስትራቴጂና ስልት በመዘርጋትና በዲጂታል ቴክኖሎጂ የታገዙ የተለያዩ የአሠራርና አደረጃጀት ሪፎርም ሥራዎችን በመሥራት ሙስናን የሚፀየፍና በጽናት የሚታገል ህብረተሰብ ከመገንባት አኳያ በቀጣይነት የትውልዱን ሥነምግባር ለማነጽ እና የሀገሪቱን የፀረ-ሙስና ትግል እንቅስቃሴ ውጤታማ ለማድረግ እንዲያስችለን በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የጋራ የሆነ የአቋም መግለጫ አውጥተናል፡፡

1. በተቋማት ሙስና እና ብልሹ አሰራር ለመከላከል ለተቋማት አመራር ሰራተኞች በሥነምግባር በማነፅ ሙስና እንዲከላከሉ የሥነምግባርና ሙስና መከላከል አቅም ግንባታ ሥልጠና እንሠጣለን፡፡ ለዚህም በሀገር አቀፍ ደረጃ ጥራትና ተገቢነት የተረጋገጠ የሥልጠና ሞጁል በማዘጋጀት በአገርዓቀፍ ደረጃ በተቋማት ውሳኔ ሰጪ ለሆኑ አመራሮች የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ስልጠና በስፋት ተደራሽ እንዲሆን እናደርጋለን፡፡

2. የፀረሙስና ትግልን ህዝባዊ ለማድረግ እንዲያግዝ በሥነምግባር ግንባታ፣ በሙስና መከላከል እና በሙስና ወንጀል ህግ ማስከበር ላይ የህዝብ ግንዛቤ ሊፈጥሩ የሚችሉና በመረጃና በማስረጃና የተደገፉ መልእክቶችን በማዘጋጀት በተለያዩ ሚዲያዎች ለህዝብ እንዲደርስ እናደርጋለን፡፡

3. በሀገር አቀፍ ደረጃ በቁጥር ከ10ሺ በላይ ለሚሆኑ የጸረ ሙስና ትግል ስኬታማነት ከፍተኛ ሚና ያላቸው የሥምግባር መከታተያ ክፍሎች ባለሙያዎችን ትስስር መድረክ በመፍጠርና የፀረ ሙስና ትግሉን በብቃት እንዲወጡ ይደረጋል፣ ለዚህም በየተቋማቱ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል አደረጃጀት እንዲጠናከር ለማድረግ እንሰራለን፡፡

4. በሀገሪቱ ቋማት ውስጥ ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ተጋለጭነት ስጋት ያላቸውን አሠራሮችን የሙስና መከላከል ጥናት በማካሄድ የማሻሻያ ምክረ ሐሣብ በማመንጨት ተግባራዊ እንዲሆን ክትትል ይደረጋል፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከተካሄዱ የሙስና መከላከል ጥናቶች ውስጥ የተመረጡትን በጋራ መድረክ በሚደረግ ጉባኤ በገምግም ቀጣይ አቅጣጫ በማስቀመጥ እንዲተገበር እንሰራለን፡፡

5. ከህዝብ በሚደርስ የሙስና መከላከል ጥቆማ መነሻነት በሂደት ያለን የሙስና ወንጀልን የአስቸኳይ ሙስና መከላከል ሥራ በመስራት፣ ሂደቱ በአፈጣኝ እንዲቋረጥ በማድረግ የተጀመረው አሠራር እንዲስተካከል እናደርጋለን፡፡

6. ለተቋማት ሙስና ለመከላከል የግልጽነትና ተጠያቂትን ለማስፈን የተቋማት ሁሉም አመራሮችና ሠራተኞች በቴክኖሎጂ ጭምር ሀብታቸውን እንዲያስመዘግቡ በማድረግ ሽፋኑን ለማሳደግ ግልፅነትና ተያቂነት እንዲረጋገጥ በትኩረት እንሠራለን፡፡

7.የሙስና ስጋት የሚስተዋልባቸውን ዘርፎች፣ ተቋማትንና ስራ ክፍሎችን በመለየት አመራርና ሠራተኞችን የሀብት ምዝገባ መረጃ ትክክለኛነትን በማረጋገጥ በሚገኘው አጠራጣሪ ልዩነቶች ላይ በፍትህ አካል በኩል አስፈላጊ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ በመላክ ትኩረት ክትትል እናደርጋለን፣

8. ህብረተሰቡ የሚገጥመውንና የሚያየውን የሙስና ወንጀል ጥቆማ ምስጢራዊነቱን በጠበቀ መልኩ የጥቆማ ቅበላ አሰራሩን በተሟላ ሁኔታ በቴክሎጂ እንዲታገዝ በማድረግ ጭምር፣ በመቀበል እና የቅድመ መረጃና ማስረጃ የማዳበር ስራዎችን በመስራት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ ለፍትህ አካል ይላካል፣ ስለሚወሰደው እርምጃም ተገቢውን ክትትል በማድረግ ውጤቱንም ለህብረተሰቡ የማሣወቅ ሥራ እንሰራለን፡፡

9. በፀረ ሙስና ትግል ላይ ሚና ካለቸው የየባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ ቅንጅታዊ አሠራርን ተግባራዊ በማድረግ በትብብርና በትስስር እንሰራለን፡፡

10.የኮሚሽኖችን የአገልግሎት አሰጣጥ ቀልጣፋና ግልጽነት ያለው እንዲሆን የአሰራር፣ የአደረጃጀት የሪፎርም ሥራዎችን በጥናት በመፈተሽ ተፅዕኖ ፈጣሪ የስነምግባር ግንባታ እና የሙስና መከላከል ተግባራትን ለማከናወን በትኩረት እንሰራለን፡፡

11. በአሁኑ ወቅት በሀገራችን ከዕለት ተዕለት የሕብረሰተሰብ አገልግሎት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ የሚስተዋለውን ሙስናና ብልሹ አሰራርን ትርጉም ባለው ሁኔታ በመከላከል በመንግስትና ሕዝባዊ ተቋማት ፈጣን የሆነ የህብረተሰብ አገልግሎት ለመስጠት እንዲስያስችል የተቀናጀ የአንድ መስኮት አገልግሎት (የመሶብ አገልግሎት) ስራዎች ተጠናክሮ እንዲቀጥል የበኩላችንነ ሚና ለመወጣት እንሰራለን፡





# ቆይታ



## ኮሚሽኑ በበጀት አመቱ በሥነምግባር ግንባታ ስልጠና ዘርፍ 75ሺ በላይ አመራርና ሠራተኞች ስልጠና የወሰዱበት እና ከፍተኛ አፈፃፀም ያስመዘገብንበት ነበር፡- ም/ኮሚሽነር ፍቃዱ ሰቦቃ፡፡

የፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ተልዕኮውን ለመወጣት የተለያዩ መንገዶችን/ አማራጮችን በመጠቀም ስራዎችን እየሰራ ይገኛል፡፡ የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ስራዎችን ከሚሰራባቸው መንገዶች ውስጥ አንዱ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሲሆን በዚህም በሁለት ሳምንት አንድ ጊዜ የሚዘጋጅ የዲጅታል ጋዜጣ በማዘጋጀት ለማህበረሰቡ ያደርሳል ፡፡ ጋዜጣው ከያዛቸው አምዕዶች ውስጥ ደግሞ ቆይታ አንዱ ነው፡፡ በዚህ ወር ዝግጅት ቆይታ ያደረገው ከፌደራል የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሥነምግባር ግንባታ ዘርፍ ም/ኮሚሽነር ጋር ሲሆን እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡



ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- ክብር ኮሚሽነር በ2017 በጀት አመት በሥነ ምግባር ግንባታ ዘርፍ ምን ምን ተግባራት ተከናወኑ?

ክቡር ም/ኮሚሽነር ፍቃዱ ሰቦቃ፡- በስነምግባር ግንባታ ዘርፍ በዋነኝነት ሶስት ነገሮች ላይ ነው ትኩረት አድርገን ስንሰራ የነበርነው፡ ፡ እነሱም የትውልድ ስነምግባር ግንባታ፣ በስነምግባርና ሙስና መከላከል ላይ ግንዛቤን መፍጠር እና በየተቋማቱ ያሉትን የስነምግባር መከታተያ ክፍሎችን አቅም በመገንባት የሚሰጣቸውን ስራ በብቃት እንዲወጡ የማድረግ ተልዕኮ አንግበን ነው ስንሰራ የነበረው፡፡

በዋነኝነት ዘንድሮ አንዱ የስነምግባር ግንባታ አስመልክቶ ከሌላው ጊዜ ለየት ባለ መልኩ የተሰራ ስራ ዘርፍ ተኮር ሞጁሎችን ማዘጋጀት ነው፡፡ በአመቱ ወደ 25 ዘርፍ ተኮር ሞጁሎችን ለማዘጋጀት ታቅዶ 26 ተዘጋጅቷል፡፡ ዘርፍ ተኮር ስንል የፌዴራል ተቋማት በሙሉ በ26 ዘርፎች እንዲደራጁ ነው የተደረገው፣ 22 ሚኒስቴር መስሪያቤቶች አሉ፣ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት እንደ አንድ ዘርፍ ተወስዷል፣ ህግ ተርጓሚ አካል( ፍርድቤቶች) እንደአንድ ዘርፍ ተወስደዋል፣ በተለይም ደግሞ ለጠቅላይ ሚኒስትር ተጠሪ የሆኑ ተቋማት አንደአንድ ዘርፍ የተወሰደው፡ ፡ የመንግስት የልማት ድርጅቶች፣ ተቋማቱ ብዙ ስለሆኑ ተጠሪነታቸው ለጠ/ሚ ጽ/ቤት ቢሆኑም ተቋማቱ ብዙ ቢሆኑም እነሱንም እንደ አንድ ዘርፍ አደራጅተናቸዋል፡፡ በተለየ ሁኔታ የሄድንበት አንዱ ህዝባዊ አደረጃጅቶች የሚባሉት እንደ አንድ ዘርፍ አደራጅተን የክትትል ስራዎችን ሰርተናል፡፡

ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡-ኮሚሽኑ ከሚሰራቸው ሥራዎች አንዱ ሥነ ምግባር ግንባታ ነው። በዚህ ዘርፍ እርስዎ መሪ ነዎት በዘርፉ በዚህ አመት መልካም እንቅስቃሴዎች እንዳሉ ይታወቃል፡፡ እነዚህን ጥሩ እንቅስቃሴዎች ቢገልጹልን?

ክቡር ም/ኮሚሽነር ፍቃዱ ሰቦቃ፡- በተለየ መልኩ ከሰራነው ስራ የትውልድ ስነምግባር ግንባታ ስኬታማ ለማድረግ 26 ሞጁሎቹ ከ9 ዩኒቨርሲቶዎች የተውጣጡ 54 ከፍተኛ ምሁራን( ዶክተሮች) አሰልጣኝ አድርገን ወስደናል፣ ሞጁሉን እንዲያዘጋጁ ኮሚሽኑ በየዘርፍ ጥናት አካሂዷል፡፡ ከዚህ በፊት ይሄንን ጥናት መሰረት ያደረገ፣ በጥናቱ ግኝት ላይ ተመስርቶ ሞጁሎች እንዲዘጋጁ ነው የተደረገው፡፡ ሞጁሎች ከተዘጋጁ በኋላ ወደ ስልጠና ከመግባታቸው በፊት የሞጁሎቹ ጥራትና ተገቢነት የመገምገም ስራ ተሰርቷል፣ ወደ ስልጠና መግባት የሚያስችል ሞጁል ተዘጋጅቷል ወይ የሚል ሁለት ጊዜ የጥራትና ተገቢነት ግምገማ ተካሂዷል፡፡ ይሄ ከተረጋገጠ በኋላ ቀጥታ ያደረግናው ከዘርፎች ጋር ስራውን መስራት የሚያስችለንን መግባባት መፍጠር ስለነበረብን 26 ዘርፎች ደብዳቤ ጽፈን፣ የፀረ-ሙስና ትግሉን በመንግስት ተቋማት ለማቀጣጠል የከፍተኛ አመራሩ ድርሻ ትልቅ በመሆኑ በጋራ እንድንሰራ የሚል ጥያቄና ነው ያቀረብነው፡፡ ጥያቄያችን ተቀባይነት በማግኘቱ በ26ቱም ዘርፎች ውጤታማ የሆኑ ስራዎችን ሰርተን አንደኛው ዘርፍ ላይ ብቻ ነው በተለያየ ምክንየት ያልተሳካልን( ህዝብ ተወካዮች ም/ቤት) እንጂ ሌሎችን ማሳካት ችለናል፡፡ የህዝብ ተወካዮች ምክርቤትም በ2018 በጀት አመት የመጀመሪያ ስራችን ማድረግ አለብን፣ በ2017 የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ላይ ማሳካት ስላልቻልን ከእረፍት ሲመለሱ የመጀመሪያ ስራችን አድርገን ነው የምንሰራው፡፡ ስለዚህ ለስልጠናው ልዩ ትኩረት በመስጠት የተቋሞቻቸው አመራር፣ ሰራተኞች ውጤታማ እንዲሆኑ በጀት በመመደብ ስለስጠናውን በበላይነት በመምራትና በመከታተል፣ ስልጠናው ሲከፈትም ሲዘጋም ከፍተኛ አመራሩ እየተገኘ መመሪያ፣ አቅጣጫ በመስጠት ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

ስልጠናውን ደግሞ በየምዕራፉ እየገመገምን ምን ጠንካራ ጎኖች እና ደካማ ጎኖች አሉ፣ የሚለውን በምዕራፍ ከፋፍለን እየገመገምን ግብረ መልስ እየሰጠን ነበር፡፡ የስልጠናውን ጥራትና ተገቢነት ለማረጋገጥ ሞጁሉ ላይ ብቻም አይደለም ስልጠናው ከተሰጠ በኋላ የአሰልጣኙ የስልጠና አሰጣጥ ሂደቱ ምን እንደሚመስል እና ምን ጠንካራ ጎኖችና ደካማ ጎኖች አሉት ተብሎ በሰልጣኞች እንዲገመገም ሲደረግ ነበር፡ ፡ አሰልጣኙ ብቻም ሳሆን ሰልጣኞች ራሳቸው የተሰጣቸውን ስልጠና ምን ያክል እውቀት ጨብጠዋል የሚለውን የብቃት ምዘና ፈተና ሲሰጥ ነው የነበረው፡፡

የስልጠናውን ጥራትና ተገቢነት ትኩረት ስለሰጠን በየሩብ አመቱ ራሱን የቻለ የስልጠና ጥራትና ተገቢነት ኮንፈረንስ ከክልሎች ጋር ጭምር ስናካሄድ ነው የነበረው፡፡ ከፌዴራል አስከ ክልል የስልጠና ጥራት ምን ይመስላል ተገቢነታቸው የሚለውን የጋራ መድረክ በመፍጠር ልምድና ተሞክሮ በመለዋወጥ ሌላ ጋር ያለውን የተሻለ ወደ ሌሎች ክልሎች እና ከተማ አስተዳድሮች ለመውሰድ እንዲያስችለን ኮንፈረንሶች ተካሂደዋል፡፡ ከክልሎችና ከተማ አስተዳድሮች ጋር 4 ኮንፈረንሶች ይካሄዳሉ ተብሎ ሶስቱን ማካሄድ ስንችል በተለያየ ምክናየት አንድ ማካሄድ አልተቻለም፡፡

እንደዘርፍ በፌዴራል ተቋማት ለከፍተኛ፣ ለመካከለኛና ለዝቅተኛ አመራሮችና ሰራተኞች ወደ ሰላሳ አምስት ሺ አምስት መቶ (35,500) ስልጠና ይሰጣል ተብሎ ታቅዶ ነበር፣ በአመቱ ሲገመገም ሰባአምሰት ሺ ስድስት መቶ ሰባ ስድስት(75,676) ማከናወን ተችሏል፡፡ የእቅዱን 213 ፐርሰንት እቅድ አፈጻጸም ማሳካት ችለናል፡ ፡ በአመቱ መጨረሻ ሲገመገም ዘርፉ ከሌላው ጊዜ በተለየ የላቀ ውጤት አስመዝግቧል፡፡ ለዚህ ውጤት መገኘት በየደረጃው ያለው አመራር ለትውልድ ስነምግባር ግንባታ ትኩረት ሰጥቶ፣ ኮሚሽኑም ደግሞ በቅርበት የክትትልና ድጋፍ በማድረግ፣ በአካል ወደታች ወርዶ በማየት፣ በየሩብ አመቱ ስልጠናውን በመገምገም፣ ከተቋማት አመራሮች ጋር በቅርበት፣ በቅንጅትና በትብብር በመስራታችን አፈጻተሙን የተሻለ አድርጎታል፡፡

ስልጠና ብቻ ሳይሆን ዜጎች የፀረ-ሙስና ትግሉ አጋር እንዲሆኑ ግንዛቤ የመፍጠር ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ ህዝቡ በትውልድ ስነምግባር ግንባታና በሙስና መከላከል ተገቢውን ግንዛቤ አግኝቶ ለፀረ-ሙስና ትግሉ የራሱን አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡

ፀረ-ሙስና ጋዜጣ፡- ሥነ ምግባር ግንባታ ሥራዎች ሲከናወኑ በተለያዩ ዘዴዎች ተደራሽ ለመሆን ይሞክራል። ኮሚሽኑ ምን ዘዴዎች ተጠቅሞ ተደራሽ ለመሆን እየሰራ ነው?

ክቡር ም/ኮሚሽነር ፍቃዱ ሰቦቃ፡- ለህብረተሰቡ ተደራሽ ለመሆን የተለያ ዘዴዎችን ተጠቅመናል፣እነሱም የፊት ለፊት መድረክ በመፍጠር፣ የኪነጥበብ ስራዎችን ደግሞ በመደበኛና በማህበራዊ ሚዲያዎች መልዕክቶች እየተቀረጹ ለህዝብ ተደራሽ ማድረግ ችለናል፡ ፡ የውይይት መድረኮች ጭምር እየተቀረጹ በመደበኛ ሚዲያ አየር ላይ እየዋሉና በማህበራዊ ሚዲያ እየተጫኑ ተደራሽ ሆነናል፡፡

እንደ ኮሚሽን በፌዴራል ደረጃ በተለየ መልኩ በአስር ዘርፎች በአገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ያሉ ችግሮች መንስኤ ምንድን ነው በሚል በተለየ መልኩ የዳሰሳ ጥናት ተደርጎ በትኩረት እንዲሰራባቸው ሰነድ በማዘጋጀት ሀገራዊ ንቅናቄ ለማድረግ ታሳቢ ያደረገ ተቋማቱ ላይ ትኩረት ተደርጎ ሲሰራበት ቆይቷል፡፡ ከአመራሩ እስከ ሰራተኛው ድረስ ሰፊ ውይይት ተደርጎ ንቅናቄ መፍጠር የተቻለበት፣ በእለት ተዕለት እንቅስቃያቸው ውስጥ የተስተዋሉ ችግሮችን ለመፍታት ርብርብ አድርገዋል፡፡

ሌላው እንደግንዛቤ ማስጨበጫ የተጠቀምንበት ከሌላው ጊዜ ለየት ባለ መልኩ አንዱ በከፍተኛ ት/ት ተቋማት የተማሪዎች ውድድር፣ የስነምግባር እና የፀረ-ሙስና እጩ አምባሳደር ዘንድ በ48 የመንግስት የኒቨርሲቲዎች ላይ ለመስራት እቅድ ይዘን ስንንቀሳቀስ አንደኛው ብቻ ነው በማጠቃለያው ሀገራዊ ውድድሩ ላይ ያልተሳተፈው፣ ሶስቱ ዩኒቨርሲቲዎች ደግሞ ማሟላት የሚገባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች ወይም የተሟላ ተወዳዳሪዎችን ይዞ ባለመምጣታቸው ከውድድር እንዲሰናበቱ ተደርጓል፡፡ ነገር ግን ውድድሩ ሲካሄድ ከታች ጀምሮ እየተካሄደ ነበር የመጣው መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ብቻ ነበረ በለያየ ምክንየት ያልተሳተፈው ፡፡

ውድድሩ ሲካሄድ ሂደቱ አንድ ዩኒቨርሲቲ በስሩ ከምፓሶች አሉት፣ ኮሌጆች አሉት፣ ስለዚህ በኮሌጅና በካምፓስ ውድድር ተካሂዶ መጨረሻ በዩኒቨረሲቲ ደረጃ ውድድሮች ተደርገው አሸናፊዎች እንዲለዩ ተደርጓል፡፡ ከተለዩ በኋላ እዛው በዩኒቨርሲቲው የበላይ አመራሮች ለእነዚህ ተማሪዎች እውቅናና ሽልማት የመስጠት ሂደት ነበረ፡፡ በሀገር አቀፍ ደረጃ ደግሞ ከአንደኛ አስከ አምስተኛ የወጡትን ተማሪዎች በመጥራት ውድድር አካሂደናል፡፡ ውድድሩ እጅግ በጣም ሳቢ የነበረ ትልቅ መነሳሳትን በተማሪዎች የፈጠረ ነበር፡፡ ኮሚሽኑ ተማሪዎች ወደ ውድድሩ ከመግባታቸው በፊት አስቀድሞ ከ650 በላይ ጥያቄና መልስ ያዘጋጀውን በድረ-ገጻችን በመለጠፍ ግንዛቤ እንዲያገኙ አድርገናል፡፡ ይሄን ያደረግንበት ምክንየት ተማሪዎቹ የማንበብና የማወቅ፣ ለውድድሩም በእሱ መሰረት እንዲዘጋጁ በሚል ሲሆን ለአገራዊ ውድድሩ ደግሞ ጥያቄዎችን ለተማሪዎቹ አዘጋጅተናል፡፡

ተማሪዎችን ወደ ውድድር ለማምጣት ምን አይነት ተማሪዎች ናቸው የሚለውን ራሱን የቻለ መመዘኛ መስፈርት ነበረው፡፡ አንዱ ተማሪዎች የስነምግባር ክበብ አባላት መሆናቸው፣

ወደ ገፅ 8 ዞሯል

